መስከረም 2 7 2012.
4/0199/12

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጉምሩክ ኮሚሽን ቁጥር 1
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Customs Commission No.1

የጉምሩክ ሥነ-ስርዓት ለሚፈጸምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ
<u>በያሉበት</u>

የገቢዎች ሚኒስቴር በቁጥር 1/48/11 ነሃሴ 30 ቀን 2012 በተጻፈ ደብዳቤ **የዕቃ ፍተሻና ቅድሚያ የጉምሩክ ሥነ-ስርዓት የሚፈጸምበትን ዕቃ** ለመወሰን የወጣውን **መመሪያ ቁጥር** 172/2013 159/2011 በመላክ ተግባራዊ እንዲደረግ አሳውቋል፡፡

በመሆኑም የዕቃ ፍተሻ እና ቅድሚያ የጉምሩክ ሥነ-ስርዓት የሚፈጸምበት ዕቃ አወሳሰን ስራዎች በመመሪያ ቁጥር 172/2013 159/2011 መሰረት ተፈጻሚ እንዲደረግ እያሳሰብኩ የመመሪያውን 10 ገጽ ኮፒ አባሪ በማድረግ የተላከ መሆኑን አሳውቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ደበሌ ቃበታ ሁርሳ
የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር

<u>ግልባጭ</u>
- ለጉምሩክ ኦፕሬሽን ዘርፍ
- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ
- ለተቋማዊ አቅምና ድጋፍ ዘርፍ

<u>ጉምሩክ ኮሚሽን</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገቢዎች ሚኒስቴር
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF REVENUES

ጉት -661
8/13/11

ቀን ነሀሴ 30 2011
Date
ቁጥር 1/48/11
Ref.No

ለጉምሩክ ኮሚሽን
<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>መመሪያ ስለመላክ፤</u>

የዕቃ ፍተሻና ቅድሚያ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት የሚፈፀምበትን ዕቃ ለመወሰን የወጣውን መመሪያ ቁጥር 172/2013 ~~159/2011~~ ከዚህ ጋር አባሪ በማድረግ የላክን ስለሆነ በመመሪያው መሠረት እንዲፈፀም አሳስባለሁ፡፡

ከሰላምታ ጋር

አዳነች አቤቤ
ሚኒስትር

<u>ግልባጭ፤</u>

- ለሕግ ተገዥነት ዘርፍ
  <u>ገቢዎች ሚኒስቴር</u>

በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን
Ethiopian Customs Commission
Records Documentation No.1

የበለፀገች ኢትዮጵያ!

Phone: +251 11 662 98 00/ 01/02/03/04/05/06/07/08 Fax: /+251 11 662 98 17
face book page: ministry of revenues. FBP: mor Ethiopia Twitter: erca@twitt
web site: http//www:erca.gov.et P.o. Box: 2559 Addis Ababa, Ethiopia

# የዕቃ ፍተሻ እና ቅድሚያ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት የሚፈጸምበትን ዕቃ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 172/2013

የገቢዎች ሚኒስቴር

ነሐሴ 2011 ዓ.ም


በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን * 1 *
Ethiopian Customs Commission Records Documentation No.1

# <u>የዕቃ ፍተሻ እና ቅድሚያ የጉምሩክ ሥነ- ሥርዓት የሚፈፀምበትን</u>

# <u>ዕቃ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 172/2013</u>

በገቢና ወጪ ዕቃዎች ላይ በሚደረግ ፍተሻና ቁጥጥር ምክንያት የሚባክነውን ጊዜ ለመቀጠብ፣ በዕቃዎች ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለማስቀረትና ቁጥጥሩን በአስተማማኝ ሁኔታ ማከናወን የሚያስችል በዕቃ መፈተሻ መሳሪያ በመጠቀም አካላዊ ፍተሻ የሚቀንስበትን ሁኔታ መወሰን በማስፈለጉ፣

በጉምሩክ ትራንዚት ሂደት ላይ ያሉና ወደ ጉምሩክ መጋዘን የገቡ ዕቃዎች ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት የሚፈጸምባቸውን እቃዎች ዓይነት መወሰን በማስፈለጉ፣

ዕቃዎችን በጉምሩክ ትራንዚት ጉዞ ወቅትና ከጉምሩክ ቁጥጥር ለነጻ ዝውውር ከሚለቀቅበት አሠራር ጋር ተያይዞ ሊፈጠር የሚችለውን ተገቢ ያልሆነ የአገልግሎት መጓተት ለማስተካከል ፈጣንና ቀልጣፋ የሆነ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣

የገቢዎች ሚኒስቴር በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 23/8 እና አንቀጽ 180(1) መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌ</u>

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

   ይህ መመሪያ "የዕቃ ፍተሻ እና ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የጉምሩክ ስነ-ስርዓት የሚፈፀምባቸውን ዕቃዎች ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 172/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>ትርጉም</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

Ethiopian Customs Commission Records Documentation No.1
Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Revenues

1/ "ቅድሚያ ተሰጥቶት የጉምሩክ ስነ-ስርዓት የሚፈጸምበት ዕቃ" ማለት በቀላሉ የሚቀጣጠል፣ የሚተን፣ የሚበላሽ እንዲሁም በመጋዘን ውስጥ በመቆየቱ በንብረት ወይም በሰው ላይ ሊያደርስ የሚችል ማንኛውንም እቃ ነው ፡፡

2/ "ቀይ የሥጋት ደረጃ" ማለት በስጋት ሥራ አመራር መስፈርት መሠረት በገቢና ወጪ ዕቃዎች ላይ የሚጣል ከፍተኛ የሥጋት ደረጃ ነው፡፡

3/ "ብርቱካናማ የሥጋት ደረጃ " ማለት በጉምሩክ ስጋት ሥራ አመራር መስፈርት መሠረት በትራንዚት ዕቃዎች ላይ የሚጣል ከፍተኛ የሥጋት ደረጃ ነው፡፡

4/ "የውጭ ፍተሻ" ማለት ከጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ወይም ጣቢያዎች ውጭ በህግ ወይም በኮሚሽኑ በተፈቀደው ቦታ የሚከናወን ፍተሻ ሲሆን ዲክላራሲዮኑ ከተከፈተበት ቅ/ጽ/ቤት ውጭ በሌላ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ወይም ጣቢያ የሚደረግ ፍተሻን ይጨምራል፡፡

5/ "ኮሚሽን" ማለት የጉምሩክ ኮሚሽን ሲሆን የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶችን ይጨምራል፡፡፤

6/ "አዋጅ"ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 (እንደተሻሻለ) ነው፡፡

7/ ሌሎች ቃላት በአዋጅና በደንቡ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ፣ከአገር በሚወጡ እና በተላላፊ ዕቃዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## <u>በዕቃ መፈተሻ መሳሪያ ስለመፈተሽ</u>

4. <u>ስለመፈተሽ</u>

1/ ወደ አገር ውስጥ በሚገባ ወይም ከአገር በሚወጣ ወይም ማናቸውም ተላላፊ ዕቃ ላይ የሥጋት ደረጃን መስፈርት መሠረት በማድረግ በጉምሩክ የዕቃ መፈተሻ መሳሪያ ፍተሻ ይደረግባቸዋል፡፡

2/ የዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 የተመለከተው ቢኖርም የሚከተሉት ዕቃዎች በዕቃ መፈተሻ መሳሪያ ፍተሻ አይደረግባቸውም፡፡

(ሀ) ማናቸውም በህይወት ያሉ እንስሳት፤

(ለ) የዲፕሎማቶች ዕቃዎች፣

(ሐ) ነዳጅን ሳይጨምር የመቀጣጠልና የመፈንዳት ባህሪ ያላቸው ዕቃዎች፣

(መ) በህግ እንዳይፈተሹ የተለዩ ዕቃዎች፣እና

(ሠ) ሌሎች በኮሚሽኑ ከፍተሻ ነፃ እንዲሆኑ የሚወሰኑ ዕቃዎች ናቸው፡፡

በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን
Ethiopian Customs Commission Records Documentation No.

5. <u>የመፈተሻ ቦታ</u>

1/ የዚህ መመሪያ አንቀፅ 5 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ወይም ከአገር የሚወጡ ማናቸውም ዕቃዎች በጉምሩክ መውጫና መግቢያ በሮች እና በተፈቀዱ የጉምሩክ መጋዘኖች እንዲሁም በመተላለፊያ መንገዶችና በመዳረሻ ቦታዎች ላይ በሚገኙ የዕቃ መፈተሻ መሳሪያዎች ይፈተሻሉ፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም አንድ ጊዜ ፍተሻ የተደረገበት ዕቃ አስገዳጅ ወይም አስፈላጊ ሁኔታ ካልተፈጠረ በስተቀር በድጋሚ በሌላ ጣቢያ በዕቃ ፍተሻ መሳሪያ አይፈተሽም፡፡

6. <u>በፍተሻ ወቅት ስለሚገኝ ልዩነት</u>

1/ በመግቢያ በር ወይም መተላለፊያ መስመር ላይ ያለው ቅ/ጽ/ቤት ወይም ጣቢያ ወደ አገር ውስጥ በሚገባ ወይም በተላላፊ ዕቃ ላይ በዕቃ መፈተሻ መሣሪያ ፍተሻ ሲያደርግ የስጋት አመላካች ሁኔታ የተገኘ እንደሆነ ከዝርዝር መግለጫ ጋር ዕቃውን በማሳጀብ ዲክላራሲዮን ለተከፈተበት ወይም ለመወጫ በር የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ወይም የጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ ያስተላልፋል፡፡

2/ ዲክላራሲዮን የተከፈተበት የጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያም የተላለፈለትን የሥጋት አመላካች ሁኔታ መሠረት በማድረግ ዕቃው ሙሉ በሙሉ በመፈተሽ የተገኘውን ውጤት በሶስት የሥራ ቀን ውስጥ ዕቃውን ላስተላለፈለት ለጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ወይም ጣቢያ ያሳውቃል፡፡

3/ ወጪ ዕቃን በተመለከተ በመሳሪያ በተደረገ ፍተሻ ልዩነት የተገኘ እንደሆነ ፍተሻውን ያደረገው የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ወይም መቆጣጠሪያ ጣቢያ ልዩነቱን በመመዝገብ በተሟላ ሰነድ የወጪ ዕቃ ዲክላራሲዮን ለተሞላበት የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ወይም የጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ ወዲያውኑ በማስተላለፍ ላኪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት የባንክ ፈቃድና የሽያጭ ሰነድ ማስተካከያ ማቅረቡ ሲረጋገጥ ዕቃው ከአገር እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት በልዩነት የተገኘው ወጪ ዕቃ የተላከለት ቅ/ጽ/ቤት ወይም መቆጣጠሪያ ጣቢያ ላኪው የወጪ ዕቃ የባንክ ፈቃድና የሽያጭ ሰነዱን በማስተካከል እንዲያቀርብ ያደርጋል፡፡

በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን
Ethiopian Customs Commission
Documentation No.1

5/ በመፈተሻ መሳሪያ ወይም በመደበኛ ፍተሻ በገቢ ወይም ወጪ ዕቃ ላይ ፍተሻ ማድረግበት ጊዜ በዕቃው ላይ ልዩነት ያልተገኘበት መሆኑን በመግለጽ የፍተሻ ባለሙያው ሪፖርት ካቀረበ በኋላ ዕቃው በሌላ ባለሙያ በድጋሚ ተፈትሾ ልዩነት የተገኘበት እንደሆነ ልዩነት የለበትም በማለት ሪፖርት ያቀረበው ባለሙያ ወይም ኃላፊ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ የተመለከተው ቢኖርም በተላላፊ የትራንዚት ዕቃ ላይ ልዩነት መኖሩ ሲታወቅ ለዕቃው የተላለፈ ትራንዚት ፈቃድ ለሰጠው ቅ/ጽ/ቤት የተገኘውን ልዩነት በማሳወቅ የሰነድ ማስተካከያ እና ተጨማሪ የቀረጥና ታክስ ዋስትና እንዲቀርብ በማድረግ ቅ/ጽ/ቤቱ ዕቃውን በአጀቢ ወደ መውጫ በር የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ወይም መቆጣጠሪያ ጣቢያ እንዲተላለፍ ያሳውቃል፡፡

## ክፍል ሶስት

## <u>አካላዊ የዕቃ ፍተሻ</u>

7. <u>ስለ አካላዊ የዕቃ ፍተሻ</u>

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4(2) የተመለከተው ቢኖርም ከፍተኛ የስጋት ደረጃ ያላቸው ወይም ከሚሽኑ የጠረጠራቸው ማናቸውም ገቢና ወጪ ዕቃዎች የሥጋት ሥራ አመራርን መሠረት በማድረግ አካላዊ የዕቃ ፍተሻ ይደረግባቸዋል፡፡

8. <u>በናሙና ዕቃ ስለሚፈተሽ</u>

1/ የሥጋት ደረጃቸው ከፍተኛ የሆኑ ዕቃዎች በዓይነታቸው ተለይተው ከተደረደሩ በኋላ ከተመሳሳይ የዕቃዎች ጥቅል ላይ አጠቃላይ ጭነቱን እንዲወክል በማድረግ የሚከተለው የናሙና መጠን እየተወሰደ የዕቃ ፍተሻ ይደረጋል፡፡

(ሀ) ከ1 እስከ 20 ጥቅል በሆኑት ላይ 4 ጥቅል፣
(ለ) ከ21 እስከ 40 ጥቅል በሆኑት ላይ 8 ጥቅል፣
(ሐ) ከ41 እስከ 60 ጥቅል በሆኑት ላይ 12 ጥቅል፣
(መ) ከ61 እስከ 80 ጥቅል በሆኑት ላይ 16 ጥቅል፣
(ሠ) ከ81 እስከ 100 ጥቅል በሆኑት ላይ 20 ጥቅል፣እና
(ረ) ከ100 ጥቅል በላይ በሆኑት ላይ ከእያንዳንዱ ተጨማሪ መቶ ጥቅል ላይ 20 ጥቅል ናሙናዎችን በመውሰድ ፍተሻ ይከናወናል፡፡

በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን
Ethiopian Customs Commission Records Documentation No.1

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም የሚፈተሸው ዕቃ የሥጋት ደረጃው ከፍተኛ ወይም መካከለኛ ወይም ዝቅተኛ ቢሆንም የዕቃው ቀረጥና ታክስ በክብደት መለኪያ የሚሰላ እንደሆነ የዕቃው ባለቤት ለዕቃዎቹ የክብደት ሚዛን መጠን ማረጋገጫ ሰነድ ያቀርባል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም በመጀመሪያ ከተወሰዱት ናሙናዎች በተደረገ ፍተሻ ልዩነት ከተገኘ በዲክላራሲዮኑ የተመዘገቡት ዕቃዎች ሙሉ በሙሉ ይፈተሻሉ፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ናሙና ሲወሰድ የተፈተሹ ዕቃዎችን ካልተፈተሹት ለመለየት እንዲቻል የሚመለከተው ባለሙያ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው ቅጽ ላይ ምልክት ማድረግ አለበት፡፡

9. <u>ድንገተኛ ፍተሻ</u>

1/ ኮሚሽኑ በስጋት ሥራ አመራር ወይም በሌላ መንገድ በሚያገኘው መረጃ ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡ፣ ከሀገር በሚወጡ ወይም በተሳላፊ ዕቃዎች ላይ ከመደበኛ ፍተሻ ውጪ ዕቃዎችን በድጋሚ ሊፈትሽ ይችላል፡፡

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት የሚደረገው ድንገተኛ ፍተሻ የሥጋት ደረጃቸው ዝቅተኛ ወይም መካከለኛ በሆኑ ዕቃዎች እንዲሁም ሰዎች ላይ ተፈፃሚ ሊሆን ይችላል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚደረግው ድንገተኛ ፍተሻ በመደበኛ ፍተሻ በተወሰዱ ናሙናዎችና በተቀሩት ዕቃዎች ላይ በድጋሚ ፍተሻ ሊያደርግ ይችላል፡፡

4/ በድንገተኛ ፍተሻ በተፈተሸ ዕቃ ላይ በድጋሚ ፍተሻ ልዩነት የተገኘ እንደሆነ አስቀድሞ ዕቃውን የፈተሸው የፍተሻ ኦፊሰር ተጠያቂ ይሆናል፡፡

5/ በድጋሚ በሚደረግ የድንገተኛ ፍተሻ የሚገኝ ልዩነት አስቀድሞ በተወሰደው ናሙና ላይ የሚገኝ ልዩነት ካልሆነ በስተቀር የፍተሻ ኦፊሰሩ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

## ክፍል አራት

## <u>የውጭ ፍተሻ</u>

10. <u>የውጭ ፍተሻ ስለመፍቀድ</u>

Customs Commission

Documentation No.1

1/ የውጭ ፍተሻ እንዲፈቀድለት የሚጠይቅ ሰው የተዘጋጀዉን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት እና ሰነዶችን በማያያዝ ዲክለራሲዮን ለተከፈተበት ቅ/ጽ/ቤት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

2/ የውጭ ፍተሻ ፈቃድ የሚሰጠው ዲክላራሲዮን በተከፈተበት የቅ/ጽ/ቤት ሲሆን፡-

(ሀ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 እና 12 መሠረት የሚደረገውን የውጭ ፍተሻ በሚመለከት የወጪ ፍተሻ የሚፈቀድላቸውን ድርጅቶች፣ዕቃዎችና ቦታዎች የስራ ሂደቱ ባለቤት ሊፈቅድ ይችላል፡፡

(ለ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 እና 12 መሠረት የሚደረገውን የውጪ ፍተሻ በሚመለከት የወጭ ፍተሻ የሚፈቀድላቸውን ድርጅቶች፣ዕቃዎችና ቦታዎች ውጪ ሲሆን የውጭ ፍተሻ ፈቃድ የሚሰጠው የጉምሩክ ኦፕሬሽን ጉዳዮች ምክትል ስራ አስኪያጅ ይሆናል፡፡

## 11. <u>የውጭ ፍተሻ የሚፈቀድላቸው ድርጅቶች እና ዕቃዎች</u>

1/ የውጭ ፍተሻ እንዲደረግ የሚፈቀድላቸው ድርጅቶች እና ግለሰቦች፡-

(ሀ) የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች፤

(ለ) የወጪ ንግድ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚ ግለሰቦችና ድርጅቶች፤

(ሐ) ክልላዊ እና አገራዊ የሆኑ የመንግስት ፕሮጀክቶች፤

(መ) አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ድርጅቶች፣

(ሠ) የልማት እና የሲቪክ ማህበራት

2/ የውጭ ፍተሻ እንዲደረግ የሚፈቀድላቸው ዕቃዎች፡-

(ሀ) የፋብሪካ ጥሬ ዕቃዎችና ኬሚካሎች እንዲሁም የተቀጣጣይነት ባህሪይ ያላቸው ዕቃዎች፤

(ለ) ነዳጅ እና የነዳጅ ውጤቶች፤

(ሐ) በቅ/ጽ/ቤቱ ወይም ጣቢያው ውስጥ ለመፈተሽ አመቺ ያልሆኑ ትልልቅ የፋብሪካ ማሽነሪዎች ወይም ለመፈተሽ አመቺ ያልሆኑ የኢንቨስትመንት ዕቃዎች፤

(መ) በአንድ አስመጪ በአንድ ጊዜ የሚመጡ እና ቁጥራቸው 20 እና ከዚያ በላይ የሆኑ አዳዲስ ተሽከርካሪዎች እንዲሁም ቁጥራቸው 40 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ባጃጆች፤

(ሠ) ማዳበሪያ፣ የእርዳታ እህል እና ሌሎች ከዚሁ ጋር በተያያዘ በብዛት መጥተው ወደብ ላይ የሚታሸጉና ወደ ሀገር የሚጓጓዙ መሰል ዕቃዎች፣

(ረ) ወጪ ዕቃዎች፤

(ሰ) የመኪና እና የህንጻ መስታወቶች፣

(ቀ) በቅ/ጽ/ቤቱ ወይም ጣቢያው ውስጥ ለመፈተሽ ለማራገፍና ለመጫን አመቺ ያልሆኑ፤

ዕቃዎች ናቸው፡፡

12. <u>የውጭ ፍተሻ ስለሚደረግባቸው ቦታዎች</u>

1/ ዲክላራሲዮን ከቀረበበት የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ወይም ከጉምሩክ ጣቢያ ውጭ በሚገኙ፡- በጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት፣ በጉምሩክ ጣቢያ፣ በመንግስት መ/ቤት፣ በድርጅት ቅጥር ግቢ፣ በመጋዘን፣ ፕሮጀክቱ በሚገኝበት ቦታ፤ በኢንዱስትሪ ፓርኮች የውጭ ፍተሻ እንዲደረግ ይፈቀዳል፡፡፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በልዩ ሁኔታ በሌሎች ቦታ ላይ የውጪ ፍተሻ እንዲደረግ ሊፈቀድ ይችላል፡፡

13. <u>የውጭ ፍተሻ የሚያደርግ ጣቢያ ወይም ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊነት</u>

1/ በዚህ መመሪያ መሠረት የውጭ ፍተሻ የሚያደርግ የጉምሩክ ጣቢያ ወይም የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የፍተሻውን ውጤት ስካን በማድረግ በሸኝ ደብዳቤ የውጭ ፍተሻ ለፈቀደው የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ፍተሻው በተጠናቀቀ በሦስት የሥራ ቀናት ውስጥ በኢሜይል ወይም በአውትሉክ ወይም በጉምሩክ ሥራ አመራር ሥርዓት መላክ አለበት፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተላከው የውጭ ፍተሻ ሪፖርት መሠረት ቀጣይ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት በአንድ ሣምንት ጊዜ ውስጥ መፈጸም አለበት፡፡

3/ የውጭ ፍተሻ የተፈቀደለት ድርጅት እና ዕቃ ከተፈተሸበት የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ወይም የጉምሩክ ፍተሻ ጣቢያ በተዘጋጀው ቅፅ መሠረት ፍተሻውን ለፈቀደው የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የውጭ ፍተሻ ሪፖርት ሳያቀርብ ሌላ የውጭ ፍተሻ ፈቃድ መስጠት የለበትም፡፡

14. <u>የውጭ ፍተሻ አፈፃፀምና ዲክላራሲዮን የተከፈተበት ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊነት</u>

1/ ማንኛውም አካላዊ የውጭ ፍተሻ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ላይ በተመለከተው በናሙና የመፈተሽ ሥርዓት መሠረት መፈጸም አለበት፡፡

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የገቢዎች ሚኒስቴር No.1
Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Revenues
በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን *1
Ethiopian Customs Commission Records Documentation No.1

2/ የውጪ ፍተሻ በሚደረግበት ዕቃ ላይ ልዩነት የተገኘ እንደሆነ በልዩነት የተገኘው ዕቃ ዲክላራሲዮን ለተከፈተበት ቅ/ጽ/ቤት እንዲተላለፍ በማድረግ ውሳኔ ይሰጥበታል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገዉ ቢኖርም በጎረቤት አገሮች በሚገኝ የጉምሩክ ማስተባበሪያ ቅ/ጽ/ቤቶች በገቢ ዕቃ ላይ በሚደረግ የውጭ ፍተሻ ልዩነት የተገኘ እንደሆነ በልዩነት የተገኘው ዕቃ ተመዝግቦ ወደ መዳረሻው ቦታ እንዲተላለፍ ከተደረገ በኋላ የፍተሻው ሪፖርት ለሚመለከተው ቅ/ጽ/ቤት ከነሰነዱ ይላካል፡፡

15. <u>የውጪ ፍተሻ ስለመከልከል</u>

ኮሚሽኑ፡-

(ሀ) የውጪ ፍተሻ እንዲደረግበት ፈቃድ ከተጠየቀበት ዕቃ ጋር የተከለከለ ወይም ገደብ የተደረገበት ወይም መግለጫ ያልቀረበበት ዕቃ ተቀላቅሎ የተጫነ መሆኑን የሚያመላክት ተጨባጭና አሳማኝ መረጃ የተገኘ እንደሆነ፣ወይም

(ለ) አስመጪው አስቀድሞ የውጭ ፍተሻ የተደረገበትን ሪፖርት ተከታትሎ ዲክላራሲዮን ሳያዘጋ የቀረ መሆኑን ያረጋገጠ እንደሆነ፣

የቀረበውን የውጭ ጥያቄ ላይቀበል ይችላል፡፡

16. <u>መረጃ ስለመያዝ</u>

በዚህ መመሪያ መሰረት ፍተሻ በሚደረግበት ጊዜ የተገኘን ማንኛውም ልዩነት እና ልዩነት የተገኘበትን አስመጪ ፣ ላኪ ወይም የጉምሩክ አስተላላፊ የሚመለከት የተሟላ መረጃ በቴክኖሎጂ የመረጃ ሥርዓት ተመዝግቦ መያዝ አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## ቅድሚያ የጉምሩክ ስነ-ስርዓት የሚፈጸምበት ዕቃ ዓይነት

17. ስለቅድሚያ አገልግሎት አሰጣጥ

1/ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት እቃዎች ወደ አገር ውስጥ ሲገቡ ወይም ከአገር ሲወጡ ዲክላራሲዮን አቅራቢው በሚያቀርበው ማመልከቻ መሠረት ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የጉምሩክ ስነ-ስርዓት እንዲፈጸምባቸው ይደረጋል፡-

(ሀ) መድሐኒቶች፣

(ለ) በቀላሉ የሚቀጣጠሉ ዕቃዎች፣

(ሐ) ጨረር አመንጪ መሣሪያዎች፣

(መ) ዘር እና ችግኞች፣

(ሠ) በሕይወት ያሉ እንስሳት፣

(ረ) ለምርመራና ለላብራቶሪ የሚውሉ ነፍሳት ወይም ዕጮች፣

(ሰ) ለወጪ ዕቃዎች የምርት ግብዓት የሚሆኑ ጥሬ ዕቃዎች፣

(ሸ) በመትነን አካባቢን የሚበክሉ ኬሚካሎች፣

(ቀ) ወቅታዊ የሆኑ መጽሔቶችና ጋዜጦች፣

(በ) ምግቦች፣አትክልቶች፣ ፍራፍሬዎችና መጠጦች፣

(ተ) ወጪ ዕቃዎች፣

(ቸ) በኮሚሽኑ የተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች እና የልዩ መብት ተጠቃሚዎች ወደ አገር ውስጥ የሚያስገባቸውና ወደ ውጭ የሚልኳቸው ዕቃዎች ፣

(ኀ) ለአንድ ተቋም መደበኛ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ እና ከዕቃዎቹ ባህሪ አንጻር ለተጠቃሚው በአፋጣኝ መድረስ ያለባቸው እና ካልገቡም በሥራው ላይ እንቅፋት የሚፈጥሩ ዕቃዎችና መለዋወጫዎች፣

(ነ) የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ ዕቃዎች፣

(ኘ) የመንግስት መ/ቤቶች፣ የመንግስት ልማት ድርጅቶች፣ ማህበራት እና የዕርዳታ ድርጅቶች የሚያስገቧቸውና የሚያስወጧቸው ዕቃዎች፣

(አ) በጉምሩክ ጊዜያዊ መጋዘን ውስጥ በማራገፍ ለመፈተሽ የማይመቹ ማሽነሪዎችና ሌሎች ተመሳሳይ ዕቃዎች፣

(ከ) ሌሎች ኮሚሽኑ የሚፈቅዳቸው ዕቃዎች፣

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 18. ስለተሻሩ መመሪያዎች

1/ የዕቃ ፍተሻ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 119/2008 በዚህ መመሪያ ተሽሯል።

2/ ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም ሰርኩላሮች እና አሠራሮች ይህ መመሪያ በሚሸፍናቸው ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም።

### 19. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ለጉምሩክ በቀረበና ተቀባይነት ባገኘ ዲክላራሲዮን የሚሸፈን ዕቃ በነበረው መመሪያ መሠረት ይስተናገዳል።



በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Customs Commission Records & Documentation No.1
የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ገቢዎች ሚኒስቴር No.1
Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Revenues

20. <u>መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በገቢዎች ሚኒስትር ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል።

አዲስ አበባ-----------------ቀን 2011 ዓ.ም.

አዳነች አቤቤ

የገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር